## ለ2022 የ“ታንክስ ጊቪንግ” ኮንፈረንስ ቁልፍ መግለጫዎች

በመላው አጽናፍ ዓለም ልዩና ብቸኛው ዘላለማዊ በረከት
በሕይወት፣ በባሕርይ እና በመገለጥ፣ ተመላኪነቱን ሳይጨምር፣ እኛን አምላክ በማድረግ ግብ
ለክርስቶስ አካል ግንባታ ግብ፣ የዘላለማዊ ኢኮኖሚውን ግብ - አዲሲቱን ኢየሩሳሌም - ለመፈጸም
በውስጣችን ባደረው እና በቅጽበት በሚሠራው የሕይወት መንፈስ ሕግ ድሰታ
ሦስታንዱ በመለኮታዊው ሥላሴው አምላክ ራሱን ወደ ውስጣችን ማደሉ ነው፡፡

መንፈስን፣ ቅዱሱን እስትንፋስ በመተንፈስ፣ አንዱን መንፈሳዊ መጠጥ፣
ክርስቶስን ሁሉን እንዳካተተ መንፈስ በመጠጣት እና
ክርስቶስን እንደ የእግዚአብሔር እንጀራ -
እውነተኛው እንጀራ፣ ሰማያዊው እንጀራ፣ እንደ የሕይወት እንጀራ በመብላት እና
እርሱን እንድንገልጥ እና እንድንወክለው በእርሱ ለመቀናበር
ሁላችንም የመለኮታዊውን ሥላሴ መለኮታዊ እደላ መለማመድ እንችላለን፡፡

ለእርሱ መሥራት የሚፈልገውን ሁሉ እንዲሠራ እድል በመስጠት፣
በክርስቶስ እንዳመኑ ሰዎች ጌታን መውደድ እና ራሳችንን ለእርሱ ክፍት አድርጎ መጠበቅ፣
እና በመለኮታዊው ኢኮኖሚ ተዓምራዊ-መደበኛነት መሠረት
በመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ
ዘወትር መደበኛ በሆኑ ልምምዶች በሕይወት መርካት ያስፈልገናል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ስድሳ ስድስት መጽሐፍት መላው መገለጥ መሠረት፣
መለኮታዊው ሥላሴ—አብ፣ ወልድ እና መንፈስ—
ለመለኮታዊው እደላ፣ ማለትም፣ ለእግዚአብሔር ወደ ተመረጡት ሕዝቡ ውስጥ መሰራጨት ነው፤
ክርስቶስ ከዘላለም እስከ ዘላለም እንዲነግሥ የዓለም መንግሥት ለጌታችን እና ለእርሱ ለክርስቶስ ስትሆን
የክርስቶስ አካል ሆነን መገንባት እንድንችል እና ለደግመኛው መምጣቱ የክርስቶስ ሙሽራ እንድንሆን
እግዚአብሔር ራሱን ወደ እኛ ውስጥ እንዲያድል፣ ራሱን በእኛ ውስጥ እንዲሠራ፣ እንድንደሰት እርሱ ሦስታንድ ነው፡፡

*© 2022 Living Stream Ministry*

**ታንክስጊቪንግ ኮንፍረንስ**
**መልእክቶች አውትላይኖች**
**ሕዳር 24-27፣ 2015**

**አጠቃላይ ርዕስ፡-**
**ለመለኮታዊው ኢኮኖሚ የመለኮታዊው ሥላሴ**
**መለኮታዊ እደላ**

መልእክት አንድ

**በመለኮታዊው ሥላሴ ወደ ውስጣችን በሚከናወነው መለኮታዊው እደላ አማካኝነት**
**ለእግዚአብሔር መለኮታዊ ኢኮኖሚ መፈጸም**
**የሦስታንዱ አምላክ ዘላለማዊ በረከት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዘኍ. 6፡22-27፤ 2 ቆሮ. 13፡14፤ ራእ. 22፡1-2

**I. በመላው አጽናፍ ዓለም ልዩና ብቸኛው በረከት ሦስታንዱ አምላክ ነው፣ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ኢኮኖሚ ለመፈጸም ይህ በረከት ለድሰታችን ወደ እኛ የሚመጣው በመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ ወደ ውስጣችን መታደል አማካኝነት ነው፡-**

ሀ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ራሱን በክርስቶስ ወደ ተመረጡት ሕዝቡ ለማደል የሆነው የቤተሰቡ አስተዳደር ነው፣ ይህም ራሱን የሚገልጥበት ቤት ይኖረው ዘንድ ነው፣ ቤቱም የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ናት፤ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ዘላለማዊው ዕቅዱ ነው፣ መለኮታዊው ዕደላው ደግሞ ዕቅዱን የሚፈጽምበት መንገድ ነው—1 ጢሞ. 1፡3-4፤ 3፡15፤ ሮሜ 12፡5፤ ኤፌ. 1፡10፤ 3፡8-9፤ 2፡10።

ለ. ለቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ አካል መገንባት እና ለሙሽራይቱ መዘጋጀት የክርስቶስን መንግሥት ለማምጣት የእግዚአብሔር መለኮታዊ እደላ፣ አማኞችን በሕይወት እና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር መለኮት ያደርጋል፤ ለዚህ ዓላማ ራሱን "ሰው ለማድረግ" እግዚአብሔር ሰው ሆነ፤ ከዚያም እኛን "እግዚአብሔር ለማድረግ" ራሱን እንደ ሕይወት ወደ ውስጣችን ያድላል።

ሐ. በኢኮኖሚው የእግዚአብሔር ውጥን በመለኮታዊው ሥላሴው—አብ፣ ወልድ እና መንፈስ—ራሱን ወደ ተመረጡት ሕዝቡ ውስጥ ማደል ነው፤ በጊዜ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ብቸኛው ግብ ዕለት ዕለት ራሱን ወደ ውስጣችን ማደል ነው።

**II. በዘኍልቁ 6፡22-27 በካህናት የመባረክን ምሳሌ እናያለን፤ ይህ በረከት የብሉይ ኪዳን በረከት ወይም የአዲስ ኪዳን በረከት አይደለም፤ ይልቁንም የሦስታንዱ አምላክ ዘላለማዊ በረከት ነው፣ ይህም ሦስታንዱ አምላክ በመለኮታዊ ሥላሴው ለድሰታችን ራሱን ወደ ውስጣችን ማደሉ ነው፡-**

ሀ. "እግዚአብሔር ይባርክህ፥ ይጠብቅህም" ለአብ ሊሰጥ ይችላል—ቁ. 24፡-

1. አብ በእያንዳንዱ መንገድ እና በእያንዳንዱ ገጽታ በፍቅሩ ይባርከናል (ተዛ. ኤፌ. 1፡3)፣ በእያንዳንዱ መንገድ እና በእያንዳንዱ ገጽታ በኃይሉ ይጠብቀናል (ተዛ. ዮሐ. 17፡11፣ 15)።
2. ጌታ አብ በስሙ እንዲጠብቀን ጸለየ (ቁ. 11)፤ ይህም በሦስታንዱ አምላክ እደላ ውስጥ እንዲጠብቀን ነው፤ ጌታ ኢየሱስ አብ ከክፉው ይጠብቀን ዘንድ መጸለይን ቀጠለ (ቁ. 15)።
3. ሙሉ በሙሉ በሦስታንዱ አምላክ እደላ ውስጥ ለመጠበቅ እና ሙሉ በሙሉ ከክፉው ክልል ውጭ ለመሆን በረከት መጸለይ አለብን፤ ይህ ምን ዓይነት በረከት ነው!

ለ. "እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፥ ይራራልህም" ለወልድ ሊሰጥ ይችላል—ዘኍ. 6፡25፡-

1. በሉቃስ 1፡78 ጌታ ኢየሱስ ሊወለድ ሲል ዘካርያስ "የንጋት ፀሐይ ከሰማይ ወጣችልን" (አ.መ.ት.) ብሎ ትንቢት ተናገረ፤ የንጋት ፀሐይ በመለኮታዊው ሥላሴ ውስጥ ወልድ ነው፤ ይህ በሚያበራ መንገድ ራሱን ለእኛ ለማሳየት የሆነውን የእግዚአብሔርን ተሠግዎ ያመለክታል—ማቴ. 4፡16፤ ዮሐ. 8፡12።
2. በዘኍልቁ 6፡25 *ፊቱን* የሚለው ቃል መገኘትን ያመለክታል፤ ፊቱን በእኛ ላይ እንደሚያበራው ማንነት ክርስቶስ ወልድ የማይታየው አምላክ የሚታይ መገኘት ነው—2 ጴጥ. 1፡16-18፤ ማቴ. 17፡1-2።

3. ዘኍልቁ 6፡25 ያሕዌ ፊቱን በእኛ ላይ ማብራቱን ብቻ ሳይሆን ያሕዌ ለእኛ መራራቱንም ጭምር ይናገራል፤ እነዚህ ሁለት ነጥቦች በአንድ ላይ ሲደመሩ ከዮሐንስ 1፡14፣ 16-17 ጋር እኩል ይሆናሉ።
4. የእግዚአብሔር ተሠግዎ የመገኘቱ ማብራት ነበር፣ ከዚህ ማብራት ጋር አብሮ ጸጋ ነበር፤ ይህ ጸጋ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ነው፣ ይህም በእርግጥ ክርስቶስ ራሱ ነው—2 ቆሮ. 13፡14።

ሐ. "እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ፥ ሰላምንም ይስጥህ" ለመንፈስ ሊሰጥ ይችላል—ዘኍ. 6፡26፡-

1. ፊት የሰውዬውን መገኘት ያመለክታል፣ የፊት ገጽታ ደግሞ የሰውዬውን መገለጥ ያመለክታል፤ የራስን የፊት ገጽታ ወደ አንድ ሰው ላይ ማንሣት ማለት ለዚያ ሰው ማጽናት፣ ማረጋገጥ፣ ቃል መግባት እና ሁሉን ነገር መስጠት ነው።
2. ኢየሱስ እንደ የእግዚአብሔር ፊት መጣ፣ መንፈስ ቅዱስ እንደ የእግዚአብሔር የፊት ገጽታ ይመጣል፤ ካሳዘንነው የፊቱ ገጽታ ይጠቁራል (ኤፌ. 4፡30)፣ ከታዘዝነው ግን በእኛ ይደሰታል፣ ለእኛም ለማጽናት፣ ለማረጋገጥ፣ ዋስትና ለመስጠት፣ ቃል ለመግባት እና ሁሉን ነገር ለመስጠት ፊቱን ያነሣል።

## III. በሁለተኛ ቆሮንቶስ 13፡14 ላይ ያለው በረከት በዘኍልቁ 6፡22-27 ላይ ካለው በረከት ጋር አንድ ነው፤ ይህ የሦስታንዱ አምላክ ዘላለማዊው በረከት ነው፣ እርሱም ሦስታንዱ አምላክ በመለኮታዊ ሥላሴው ለድሰታችን ራሱን ወደ ውስጣችን ማደሉ ነው—"የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን"፡-

ሀ. "እግዚአብሔር ይባርክህ፥ ይጠብቅህም" እንደ የሕይወት እና የብርሃን ምንጭ የእግዚአብሔር አብ ፍቅር ነው—ቁ. 24፤ መዝ. 36፡8-9።

ለ. "እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፥ ይራራልህም" እንደ የእግዚአብሔር ቤት ስባት የክርስቶስ ጸጋ ነው—ዘኍ. 6፡25።

ሐ. "እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ፥ ሰላምንም ይስጥህ" እንደ የእግዚአብሔር ደስታዎች ወንዝ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ነው—ቁ. 26።

## IV. የጌታ ጸጋ ለድሰታችን ጌታ ራሱ ለእኛ እንደ ሕይወት ነው (ዮሐ. 1፡17፤ 1 ቆሮ. 15፡10)፣ የእግዚአብሔር ፍቅር እንደ የጌታ ጸጋ ምንጭ እግዚአብሔር ራሱ ነው (1 ዮሐ. 4፡8፣ 16)፣ የመንፈስ ኅብረት ለመሳተፋችን ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር እንደ የጌታ ጸጋ መተላለፍ መንፈስ ራሱ ነው—2 ቆሮ. 13፡14፡-

ሀ. በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14 የጌታ ጸጋ በመጀመሪያ የተጠቀሰው ይህ መጽሐፍ የክርስቶስን ጸጋ የሚመለከት መጽሐፍ ስለሆነ ነው—1፡12፤ 4፡15፤ 6፡1፤ 8፡1፣ 9፤ 9፡8፣ 14፤ 12፡9።

ለ. መንፈስ ቅዱስ እንደ የክርስቶስ ጸጋ ከአብ ፍቅር ጋር መፍሰሱ፣ መተላለፉ በክርስትና ሕይወታችን እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወታችን አቅርቦት ነው፡-

1. መላው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14 ላይ ይመረኮዛል።
2. በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14 ላይ እንደ ተገለጠው በውስጣችን ያለው የመለኮታዊው ሥላሴ ፍሰት መንፈሳዊ ትርታችን ነው።

ሐ. በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14 ላይ ባለው የሐዋርያው ጳውሎስ በረከት ውስጥ ሦስታንዱ አምላክ ወደ ሰዎች የሚመጣው ለድስታቸው ነው፤ ጳውሎስ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ማምጣት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም ወደ ውስጣቸው አመጣ፡-

1. በአንድ በኩል፣ ሌሎችን መባረክ እነርሱን ወደ እግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ማምጣት ነው፤ በሌላ በኩል፣ ሦስታንዱን አምላክ—አብን፣ ወልድን እና መንፈስን—እንዲደሰቱ እግዚአብሔርን እንደ ፍቅር፣ ጸጋ እና ኅብረት ወደ ውስጣቸው ማምጣት ነው።
2. ፍቅር፣ ጸጋ እና ኅብረት ለድሰታችን ሦስቱ የእግዚአብሔር ደረጃዎች ናቸው—ፍቅር በውስጣችን ነው፣ ጸጋ ፍቅር ሲገለጥ ነው፣ ኅብረት የጸጋ ወደ ውስጣችን መተላለፍ ነው።
3. እግዚአብሔር መነሻ ስለሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር ምንጭ ነው፤ ጌታ የእግዚአብሔር መገለጥ ስለሆነ የጌታ ጸጋ የእግዚአብሔር ፍቅር መተላለፊያ መንገድ ነው፤ የመንፈስ ኅብረት ሦስታንዱን አምላክ—አብን፣ ወልድን እና መንፈስን ከመለኮታዊ ሰናይ ባሕርያታቸው ጋር ለመለማመዳችን እና ለድሰታችን ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር የጌታ ጸጋ መተላለፍ ነው።
4. በቅዱሱ ቃል ውስጥ ያለው የመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ መገለጥ በሐዋርያው በረከት ለቆሮንቶስ አማኞች እንደተመለከተው እኛ እንደተመረጡ እና እንደተዋጁ ሕዝቡ በሂደት ባለፈው በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ አሁን እና ለዘላለም እንድንሳተፍ፣ እርሱን እንድንለማመደው፣ እንድንደሰተው እና የራሳችን እንድናደርገው እግዚአብሔር በምሥጢራዊው እና እጹብ ድንቅ በሆነው መለኮታዊ ሥላሴው እንዴት ራሱን ወደ ተመረጡት

ሕዝቡ እንደሚያድል እንድንገነዘብ እንጂ ለስነ-መለኮታዊ ጥናት አይደለም፤ የኢየሱስን ምስክር፣ ብዙዎች የተካተቱበትን የኢየሱስ መገለጥ ማግኘት ለሆነው ለእግዚአብሔር የልብ መሻት መፈጸም በአጽናፍ ዓለም ውስጥ እንዳለው ልዩና ብቸኛ በረከት እርሱን ወደ ሌሎች ውስጥ እንድናድል በሂደት ያለፈውን እና በውስጥ የሚፈሰውን ሦስታንዱን አምላክ ዕለት ዕለት መደሰት እና በእርሱ መባረክ አለብን—ቁ. 14፤ ገላ. 3፡14፤ ዘፍ. 12፡2፤ ፊልጵ. 1፡25፤ ራእ. 1፡2፣ 9-12።

**V. በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም "ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣ...እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቅ...የሕይወት ውኃ ወንዝ ...በወንዙም ወዲያና ወዲህ በየወሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ" አለ—22፡1-2፦**

ሀ. በዘላለም ውስጥ በዙፋን ላይ የተቀመጠው አምላክ ለአቅርቦታችን እና ለእርካታችን የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሕይወት ዛፍ ጋር ከዙፋኑ የሚወጣው በጉ-አምላክ፣ የሚዋጀው አምላካችን ነው።

ለ. ከተማይቱን በእግዚአብሔር ክብር፣ በመለኮታዊው ብርሃን መገለጥ ለማብራት በጉ እንደ መብራት ብርሃን በሆነው በእግዚአብሔር ያበራል—21፡23; 22፡5።

ሐ. በሕይወት ውኃ ወንዝ እንደ ምልክት የታየው ሦስታንዱ አምላክ—እግዚአብሔር፣ በጉ እና መንፈስ—በራስነቱ ሥር (በዙፋኑ ሥልጣን እንደተመላከተው) ወደ ተዋጁት ሕዝቡ ውስጥ ራሱን ያድላል።

መ. የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መንገድ ንጹሕ ወርቅ ነው (21፡21)፣ የሕይወት ውኃ ወንዙ በመንገዱ መካከል ይፈሳል (22፡1)፤ ወርቅ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ እንደ ምልክት ስለሚያሳይ፣ በእግዚአብሔር ለተዋጁት ሕዝብ የዕለት ዕለት ሕይወት እንደ ልዩና ብቸኛ መንገድ መለኮታዊው ሕይወት በመለኮታዊው ባሕርይ ውስጥ እንደሚፈስ ማየት እንችላለን።

ሠ. እንደ የመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ መጠናቀቅ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም እግዚአብሔር ራሱ በመለኮታዊው ሥላሴው—አብ፣ ወልድ እና መንፈስ—ከተመረጡት፣ ከተዋጁት፣ ዳግም ከተወለዱት፣ ከተለወጡት እና ከከበሩት ሕዝቡ ጋር እንደ ዘላለማዊ በረከታቸው ተጣምሮ፣ ተዋሕዶ እና ተካትቶ ናት፤ እንዲህ ያለው በረከት በዘኍልቁ 6 ለእስራኤል የሆነው የእግዚአብሔር በረከት ከፍተኛው-የመጨረሻው-ምርጡ ፍጻሜ ነው—ተዛ. ራእ. 21፡3፣ 12፣ 14፣ 22፤ 22፡1-2።

**VI. *"አንዳንድ ጊዜ ሁኔታችንን ስናጤን ተስፋ ልንቆርጥ እና ምንም ነገር እንደሌለን ሊሰማን ይችላል። ከፀሐይ በታች እና በመንፈሳዊው መስክ ላይ ያለው ነገር ሁሉ የከንቱ ከንቱ ሊመስለን ይችላል። የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ሳይቀር የትኛውም ነገር እውነታ እንዳልሆነ ሊሰማን ይችላል። እንዲህ ዓይነት ስሜት ሲሰማን ምን ማድረግ አለብን? ወደ ሦስታንዱ አምላክ መዞር አለብን። እርሱ እውነተኛው በረከታችን እና ድርሻችን ነው። እንደ በረከት እርሱ ያለን መሆናችን ምን ዓይነት በረከት ነው! ፊቱ፣ መገኘቱ እና እንደ ጸጋ እርሱን በየዕለቱ መደሰት ያለን መሆናችን ምን ዓይነት በረከት ነው! የበለጠ መከራ በተቀበልን መጠን እርሱን የበለጠ እንደ ጸጋ እንደሰተዋለን። የፊቱ ገጽታ በእኛ ላይ ፈገግ ማለቱ፣ ለእኛ ማረጋገጡ እና ማጽናቱ ምን ዓይነት በረከት ነው! በእርሱ ውስጥ፣ በእርሱ አማካኝነት እና ከእርሱ ጋር ሰላም ያለን መሆናችን ምን ዓይነት በረከት ነው! ሦስታንዱ አምላክ እንደ በረከታችን ይህ ነው። አ፣ የክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር እና የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከሁላችሁም ጋር ይሁን!"*— Life Study of Numbers ከሚለው መጽሐፍ፣ ገጽ. 83።**

*© 2022 Living Stream Ministry*